# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

ግንቦት 24 ቀን 2009 ዓ.ም

### ኢሕአፓ በጀግናው አርበኛ በኮሎኔል አስናቀ ዕንግዳ ሕልፈተ ሕይወት የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን በቁጭት ይገልፃል !

ኮሎኔል አስናቀ ዕንግዳ መላ ዕድሜያቸውን ያሳለፉት፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት፤ ፍትኀ-ርትዕ ፤ ዴሞክራሲ ሥርዓትና ለሀገር ሉዓላዊነት ሲታገሉ ነው። በዚኽም ምክንያት የአያሌ ዓመታት እስርና መንገላታት፤ ስደትና ጉስቁልና ተፈራርቀውባቸዋል። ይኽንንም በፀጋ ተቀብለው ፤ በመርኅ ላይ የተመሰረተ ትግል ሲያካሂዱ በመኖራቸው፤ አርዓያነታቸው ለዚያ ሰማዕታዊ ትውልድ አንፀባራቂ ኮከብ ሆኖ ቆይቷል። ወደፊትም በታሪክ እየተጠቀሰ የሚኖር ነው።

ሦስቱን ተፋራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች፤ በግንባር ቀደም ሲታገሉ መኖራቸው፤ የትግል ፅናታቸው እንከን የማይወጣው መሆኑን በተግባር አስመስክረዋል። በተለይ በደርግ ዘመን ኢሕአፓ ነጻ ባወጣው አካባቢ፤ በኢሕአፓ አባልነታቸው ታጋዮችንና አገር ወዳዶችን በማሰባሰብና ለትግል በማነሳሳት ከፍተኛ ጀብዱ ፈጽመዋል። የወያኔ አገዛዝ በሥልጣን ሲሰየምና የአገራችን ህልውና አደጋ ላይ ሲወድቅ ከፋፋዩንና አምባገነኑን ሥርዓቱ በብርቱ የተቃወሙ ሲሆን ታጋይ ድርጅቶችን በማስተባበር፤ በመምከርና በማበረታት የተጫወቱት ግምባር ቀደም ሚና የሚረሳ አይደለም። በዚኽም እንኮራባቸዋለን። እንወዳቸዋለን። እናመሰግናቸዋለን። የኢትዮጵያን ሕዝብ፤ እስከ ፍፃሜ ሕይወታቸው ድረስ ከልብ እየወደዱ አልፈዋል። ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ፍቅራቸውን የገለፁት ፤ ለሥልጣን ጉጉት፤ ለሀብት ክምችትና፤ አላፊ- ጠፊ ለሚሆነው ውዳሴ ከንቱ ሳይሆን በመርኅ ላይ በተመሠረተ ጽኑ ዕምነት ላይ ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በዚህ ቀውጢ ዘመኗ፤ ኮሎኔል አስናቀ ዕንግዳን የመሰለ የቁርጥ ቀን ልጅ በማጣቷ ታዝናለች። ሀዘኗ ዕጥፍ ድርብ የሚሆነው ግን፤ ከኢጣሊያ ወረራ አንስቶ፤ እስከአሁኑ የመከራ ዘመኗ ድረስ ፀንቶ ሲታገልላት የኖረው ጀግና ልጇ፤ አስናቀ ዕንግዳ ፤ ለሀገሩ ጥርኝ አፈር ሳይበቃ መቅረቱ ነው። ይህ ደግሞ፤ ቁጭታችንና ብስጭታችንን የበለጠ ያጠነከረዋል። ትግላችንን አጠንክረን እንድንቀጥልም ግፊት ይሆነናል። የአርበኛው ጀግና ክሎኔል አስናቀ እንግዳን ታሪክ የምናከብረው ትግላችንን በመቀጠል እንጅ፤ የሀዘን እንባ በመርጨት አይደለም። ኮሎኔል አስናቀ፤ መስዋዕትን እንጅ ፤ ማልቀስን አላስተማሩምና !

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website [www.eprp.com](http://www.eprp.com)**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ  የጀግና ልብና  የብርጉ አዕምሮ ባለፀጋ ስለነበሩ የበርካታ መፃህፍት ደረሲም ነበሩ። ልዩ-ልዩ አረዕስትን ያከተቱ  መጽሐፍትን ለአንባብያን አበርከተዋል።   ጸሐፊም ብቻ ሳይሆኑ የተዋጣላቸው አንባቢም ነበሩ። የዕድሜ ባለፀጋ ሆነው በዚህች ዓለም ጤናማ ሆነው ሕይወት እንዲኖሩ ካደረጓቸው መሠረታዊ ምክንያቶች መካከል፤   በአካል፤ በመንፈስና በአዕምሮ ጤናማ በመሆናቸው ነበር።   እነኝህ ባህርያት፤ በህይወታቸው የተፈራረቁባቸውን እንግልትና ችግር በብቃት ለመወጣት አስቸለዋቸዋል። ተክለ ስብዕናቸውም   ሊመሠረት የቻለው በዚህ ምክንያት እንደሆነ አንጠራጠርም ።

ኢ. ሕ. አ. ፓ. ኮሎኔል አስናቀ ዕንግዳን  በክብር ሲሸኝ ፤ ከታላቅ ክብርና ምስጋና ጋር ነው።፤ ለቤተባቸውና ለወዳጆቻቸው መጽናናትን እንመኛለን።